EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የምግብ ደህንነት በሁላችን ኃላፊነት

**ታምራት ተስፋዬ**

የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011፣ “መከለስ” ማለት የአንድን ምርት ግዝፈት ወይም ክብደት ለመጨመር፣ ጥራቱን ወይም ጥንካሬውን ለመቀነስ ወይም ለመጨመር፣ እይታው የተሻለ ወይም የበለጠ እንዲሆን በማስመሰል ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ዓላማ ሲባል ባዕድ ነገር ወይም ይዘት መጨመር ወይም የምርቱን ይዘት በሌላ ንጥረ-ነገር መተካት ነው ይላል።

ይህንን ብያኔ ይዘን የምግብ ክለሳ ምንነት ስናይ የምግብ ክለሳ ማለት ለንግድ ወይም በሌላ መንገድ ለኅብረተሰቡ አገልግሎት በሚቀርብ ምግብ ላይ ሌላ ባዕድ ነገር በመጨመር ወይም ይዘቱን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በሌላ ነገር በመተካት ወይም በተገቢው መንገድ በንጽሕና ባለመመረቱና ባለመያዙ ከባዕድ ነገር ጋር እንዲነካካ ማድረግ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በምግብ ክለሳ ጊዜ የምግቡን ጣዕም፣ ተፈጥሮዓዊ ይዘትና መጠኑን በመቀየር የምግቡን ጥራትና ደኅንነት በከፍተኛ ሁኔታ ለብልሽት ይዳርጋል። የምግብ መከለስ በግለሰቦችም ሆነ በማኅበረሰብ ጤና ላይ ዘርፈ ብዙ የጤና ጉዳቶችን ያስከትላል።

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን የምግብ ኢንስፔክሽንና ሕግ ማስፈጸም መሪ ሥራ አስፈጻሚ ሙላቱ ተስፋዬ እንደገለጹትም፣ ምግብ በዓለም አቀፍ የንግድ ምህዋር ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስድ ነው። ከእርሻ እስከ ጉርሻ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆን አለበት። የምግብ ደህንነት ጉዳይም በተለይ ከባለፉት ሰባት ዓመታት ወዲህ እጅግ ከፍተኛ ትኩረት የሚሠጠው አጀንዳ በመንግሥት የ2023 የዘላቂ ልማት ግቦች ውስጥ ስድስቱ ከምግብ ደህንነት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ናቸው፡፡

የምግብ ደህንነት በተለይ የምግብ ዋስትናም ሆነ የተመጣጠነ ምግብ ተደራሽነት ጋር አብሮ ሊታሰበብት የሚገባ ነው፡፡በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ የምግብ ደህንነት በተለይ ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር የመቀላቀል፣ ሕገ ወጥ የምግብ ዝውውር፣ ምግብ ላይ የሚሠሩ ወንጀሎች ወይም FOOD CRIME የበርካታ ሀገራት ራስ ምታት ሆኗል፡፡

በኢትዮጵያም፣ የምግብ ደህንነት ምንጫቸው የማይታወቅ ሕገ ወጥ በሆነ መልኩ የተመረቱና ወደ ሀገር የገቡ የምግብ ምርቶች አሳሳቢ ስጋት ናቸው። መንግሥት ኅብረተሰቡን በምግብ ደኅንነት ከሚከሰቱ የምግብ ወለድ በሽታዎችና ሌሎች በምግብ ብክለት ከሚከሰቱ ችግሮች ለመከላከል በአዋጅ ቁጥር 1112/2011 ለኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣንና ለክልል ተቆጣጣሪ አካላት ኃላፊነት ሰጥቷል፡፡

በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት በመከለሱ ወይም በሌላ ሕገ ወጥ ድርጊት ምክንያት ሞት፣ ሕመም፣ የአካል ጉዳት፣ የጤና መታወክ ወይም ሌላ የጤና ችግር ያስከተለ ምርትን ወይም ይዘትን ይለያል፤ በናሙናው ላይ ጥናት ያደርጋል፣ ውጤቱን መሠረት በማድረግ አስፈላጊውን ሕጋዊ ርምጃ እንደሚወስድ በግልፅ ተቀምጧል፡፡

እንደ አቶ ሙላቱ ገለጻ፣ የምግብ ክለሳ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት የሚችል ሲሆን ያልተገባ ጥቅም ለማካበት በማሰብ፣ በቸልተኝነት ወይም በማምረት፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝና ለሽያጭ በማቅረብ ሂደት ተገቢውን የጥራትና ደህንነት ጥንቃቄ ባለማድረግ ሊከሰት ይችላል።ይህንን ተከትሎም ተጠቃሚው ኅብረተሰብ ለመታለል፣ ለመጭበርበር ለጤና መቃወስ ያጋልጣሉ፡፡ለሞት፣ ለካንሰር፣ ለልብ ሕመምና ሌሎችም ከባድ የጤና እክሎች ይዳርጋሉ፡፡

በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ቁጥጥርን ለማጠናከር የምርት ምዝገባ፣ የመልካም አመራር ሥርዓትን በማስተግበርና የምግብ ደረጃዎችን ማስከበር ጨምሮ ውጤታማ የሚባሉ ተግባራትን እያከናወነ ቢሆንም ከምግብ ዘርፉ አድማስ ስፋነትና ከጊዜ ወደ ጊዜ በአይነትም በረቂቅነቱም እየጨመረ ከመጣው ሕገ ወጥ ተግባር አንጻር ከተጠቃሚው ጀምሮ ሁለንተናዊ ቅንጅት ወሳኝ ስለመሆኑ ነው ያሰመሩበት።

‹‹ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የምግብ ደህንነትን ለማስጠበቅ የሶስት ዓመት እቅድ ነድፎ እየሠራ ነው፣ ለአብነትም ‹‹የሚዘገበውን ምግቦች ቁጥር በመጨመር ረገድ ከ 6 ሺ ወደ 11 ሺ፣ የቁጥጥር አቅምን ወደ100 በመቶ ለማድረስ አቅዶ እየተንቀሳቀሰ ነው›› ብለዋል፡፡



**አቶ ሙላቱ ተስፋዬ**

እንደ መሪ ሥራ አስፈፃሚው ገለፃም፣ ችግሩን ለመከላከል መወሰድ ያለበት የተለያዩ መፍትሄዎችን መከተል ይገባል። ለአብነትም አመጣጡ የማይታወቅ የምግብ ምርትን መጠቀም ሊቆም የግድ ይላል፡፡ምርት ከየት ተነስቶ የት እንደደረሰ በአግባቡ ማወቅና ይህን በአግባቡ በመረጃ አስደግፎ ማቅረብና መያዝ ተገቢ ነው፡፡ከሁሉ በላይ የምግብ ደህንነትን ለማረጋገጥ የመልካም አምራችነትን መንገድ መከተል ተገቢ ነው።

ግብርናን ጨምሮ ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ምርት እና ምርታማነት ለማስጨመር ተባዩን ለማጥፋት ጥቅም ላይ የሚውሉ የማዳበሪያ ኬሚካሎች አጠቃቀም በየጊዜው በአግባቡ መከታተል ይኖርባቸዋል። ተቆጣጣሪው አካልም አስቀድሞ ሥራዎችን መሥራት አለበት። የምግብ ጥራትና ደህንነት ለመመርመር የሚያስችል ጠንካራ አቅም መገንባት ለእዚህም የሚያስፈልጉ ባለሙያዎችን ማብቃት፣ መሳሪያዎች በአግባቡ ማማሟላት ተገቢ ነው፡፡

‹‹በሌሎች ሀገራት የመንገድ ዳር የምግብ ንግድ ሳይቀር እውቀትና የሙያ ማረጋገጫን የግድ የሚል ነው። ከፋይናንስ ጀምሮ ሁለንተናዊ አቅምንም ይጠይቃል››ያሉት አቶ ሙላቱ፣ ይሁንና በኢትዮጵያ የምግብ ዘርፉ ማንም እንደፈለገ የሚገባበት ሲሆን፤ እንደሚስተዋለው ይህም መታረም እንዳለበትና ፈቃድን ጨምሮ በሌሎች የሕግ ማሕቀፎች የታጀበ ሊሆን እንደሚገባ አፅንኦት ሰጥተውታል፡፡

ይህ ማለት ግን ከምግብ ደህንነት አንፃር ጠንካራ የሕግ ማሕቀፍ የለም ማለት እንዳልሆነ ያስገነዘቡት አቶ ሙላቱ፤ ይሁንና የሕግ ማሕቀፎችን በአግባቡ በማስተግበር ረገድ ኃላፊነት የጣለባቸው ባለድርሻ አካላት ሚና መደራረብና የቅንጅታዊ አሠራር ድክመት እንዳለባቸው ነው የጠቆሙት። ይህም የቁጥጥር ሥራ ላይ ጫና የሚያሳድር በመሆኑ ቅንጅታዊ አሠራሩ ሊፈተሽ ሊስተካከል እንደሚገባ አስምረውበታል፡፡

ምግብን ከባዕድ ነገር ጋር በመቀላቀል ምክንያት የሚከሰት በሽታን ብሎም ሞትን ለመከላከል ከእርሻ እስከ ጉርሻ እንዲሁም ከእርባታ እስከ ገበታ ያለውን የምግብ ደህንነት ሥራ ኅብረተሰቡ በየደረጃው እንዲያረጋግጥ መገናኛ ብዙኃን ግንዛቤ በመፍጠር ረገድ የድርሻቸውን ሊወጡም ይገባል፡፡

ከመገናኛ ብዙኃን ባሻገር ሸማቹ ምርቶቹን ሲገዛ ከተለምዶው የተለዩ መጥፎ ባሕሪያትን የሚያሳይ ከሆነ ምግቡን ከመጠቀም መቆጠብ በተለይም ምግቦቹ የጣዕም፣ የይዘት፣ የመጠንና የሽታ ልዩነት ካላቸው፤ የምግብ ክለሳ ችግሮች ሲያጋጥሙ/ሲከልሱ ወይም እንደእዚህ አይነት መሰል ጥርጣሬዎች ሲኖር ለባለሥልጣን ወይም ለክልል ተቆጣጣሪ አካላት ጥቆማ በማቅረብ የዜግነት ድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/